COMMUNITY CHARTER SCHOOL OF CAMBRIDGE

# የካምብሪጅ ማህበረሰባዊ ቻርተር ትምህርት ቤት የቅበላ/ምዝገባ ፖሊሲ

617 354-0047 **P**
617 354-3624 **F**
enrollment@ccscambridge.org **E**
245 ቤንት ጎዳና
ካምብሪጅ, MA 02141
www.ccscambridge.org

## A. መግቢያ

የካምብሪጅ ማህበረሰባዊ ቻርተር ትምህርት ቤት (ሲሲኤስሲ) በማመልከቻ ማስገቢያ ወቅት የማሳቹሴትስ ነዋሪ የሆኑ ተማሪዎች ማመልከቻዎችን በሙሉ ያስተናግዳል። በትምህርት ቤቱ ቅበላ ለማግኘት አመልካቾች የማሳቹሴትስ ነዋሪ መሆን አለባቸዉ። ሲሲኤስሲ ከስድስተኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሚያስተምር ሲሆን አዳዲስ ተማሪዎችን የሚቀበለዉ ከ6ኛ እስከ 9ኛ ብቻ ነዉ። ትምህርት ቤቱ በየዓመቱ በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የሚኖሩትን ነባር ተማሪዎች እንዲሁም የክፍሉን አቅም ካገናዘበ በኋላ ክፍት ቦታዎችን ለይቶ ያስቀምጣል። ትምህርት ቤቱ የሎተሪ ማመመልከቻ ቅፁን በትምህርት ቤቱ ድረ-ገፅ እና በእንግዳ መቀበያዉ በኩል ለአመልካቾች ክፍት ያደርጋል። የሲሲኤስሲ የቅበላ ሂደት ከካምብሪጅ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ዲስትሪክት ጋር የተጣመረ አይደለም።

## B. የቅበላ መስፈርቶች

በሲሲኤስሲ የሚደረገዉ ምዝገባ ከአድልዎ ነፃ ሲሆን ለማሳቹሴትስ ነዋሪዎች እና በሲሲኤስ ዉስጥ እያሉ በማሳቹሴትስ ነዋሪነታቸዉ ለሚቀጥሉ ወደ 6ኛ፥ 7ኛ፥ 8ኛ እና 9ኛ ለሚገቡ ተማሪዎች ክፍት ነዉ። ተማሪዎች ለቅበላ ብቁ ለመሆን ማሟላት ያለባቸዉ ሁለት መስፈርቶች፡

1. ወላጆች/አሳዳጊዎች ማመልከቻ በሚያስገቡበት ወቅት የነዋሪነት ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ ከሚከተሉት ሰነዶች ዉስጥ አንዱን አያይዘዉ እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ።
   a. ባለፉት 60 ቀናት ዉስጥ የተሰጠ የአገልግሎት ደረሰኝ ። ተቀባይነት ካላቸዉ የአገልግሎት ደረሰኞች መካከል የስልክ፥ የነዳጅ፥ የመብራት ወይም የኬብል ቲቪ የሚጠቀሱ ሲሆን የሞባይል ስልክ ክፍያዎች ተቀባይነት የላቸዉም።
   b. ባለፉት 60 ቀናት ዉስጥ የተሰጠ የዉሃ ክፍያ ወይም የእዳ ዉዝፍ ሰነድ።
   c. በማመልከቻዉ ቀን ተቀባይነት ያለዉ የሆነ የኪራይ/የሊዝ ዉል።

   ቤተሰቦች የነዋሪነት ማረጋገጫ ካላቀረቡ ወይም የሀሰት የመኖርያነት ማረጋገጫ ካቀረቡ ማመልከቻቸዉ ዉድቅ ይሆናል፤ ቅበላ ያገኙበት ሰነድ ይሰረዛል እና/ወይም ተማሪዉ ከምዝገባ ይፋቃል/ይሰረዛል።

   ቤት-አልባ የሆኑ አመልካቾች ለቅበላ ማመልከት የሚችሉ ሲሆን ማመልከቻቸዉ ከሌሎች ማመልከቻዎች እኩል የሚገመገሙ ይሆናል። በመጠለያዎች፥ በሞቴሎች ወይም በኢኮኖሚ አቅም ማነስ ምክንያት በሌሎች ሰዎች ቤት በጥገኝነት የሚኖሩትን ቤት-አልባ አመልካቾችን ለማሳተፍ ሲባል በቤት-አልባነት የሚያመለክቱ አመልካቾች ቤት አጥነታቸዉ የሚኪኒ-ቬንቶ የቤት-አልባ ድጋፍ ደንብ ላይ የተመለከዘ መሆን አለበት። በነዋሪነት ላይ የተመሰረተ ቅበላን ለመደገፍ ሲሲኤስሲ በዝርዝር ሂደት ዉስጥ ቤት-አልባ ተብለዉ ሊወሰዱ ከሚችሉ ተማሪዎች የነባር ወይም የጊዜያዊ የነዋሪነት ማረጋገጫን ይሰበስባል።

2. በቅበላዉ ዓመት ተማሪዎች ትምህርት ከመጀመራቸዉ በፊት ያለፈዉን ክፍል ዉጤት ማለፍ ይኖርባቸዋል። ተማሪዉ በቀደመዉ አመት የክፍል ዉጤት በሚገባ ማለፉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያለቀረቡ ወላጆች/አሳዳጊዎች በዋናዉ ማመልከቻ እና የምዝገባ ሰነድ ላይ በተቀመጠዉ የስልክ ቁጥር እንዲሁም የፖስታ አድራሻ ማሳሰቢያ የሚደርሳቸዉ ሲሆን የቅበላ ጥያቄያቸዉም ይሰረዛል።

COMMUNITY
CHARTER SCHOOL OF CAMBRIDGE

# የካምብሪጅ ማህበረሰባዊ ቻርተር ትምህርት ቤት የቅበላ/ምዝገባ ፖሊሲ

617 354-0047 **P**
617 354-3624 **F**
enrollment@ccscambridge.org **E**
245 ቤንት ጎዳና
ካምብሪጅ, MA 02141
www.ccscambridge.org

ሲሲኤስሲ ምልምል አመልካቾችን ለመመረጥ የሚያካሂደዉ ምዘና የለም እንዲሁም ከማናቸዉም የችሎታ ምዘና ወይም ዉጤት ላይ የተመረኮዘ የቅበላ ምልከታ አይወስድም። ተቀባይነት ያገኙ ተማሪዎች ግን የክፍሉ የመመዘኛ ፈተና ካጠናቀቁ ብቻ ወደ ሚመለከታቸዉ የክፍል ደረጃ ይመደባሉ። ሁሉም ተማሪዎች በመለከቱበት የክፍል ደረጃ ቦታ አያገኙም። ተቀባይነት ያገኙ ተማሪዎች የክፍል መመዘኛዉ ዉጤት ምንም ቢሆን በሲሲኤስሲ ቦታቸዉን ይዘዉ መቀጠል ይችላሉ።

በቻርተር ትምህርት ቤቱ ዉስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የሚጎናፀፏቸዉን በጥልቀት የመማር እንዲሁም የመጠለያ እና የድጋፍ ግልጋሎት የማግኘት፥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የሆኑት ወይም ልዩ ትምህርት የሚያስፈልጋቸዉ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን መብቶችን ጨምሮ ለሁሉም አመልካቾች መብቶቹ በፅሁፍ እንዲደርሳቸዉ ይደረጋል። ይህ መረጃ በሎተሪ ማመልከቻዉ፥ በመጀመርያ የቅበላ ቅፅ፥ በሚወጡ እትሞች ላይ፥ በትምህርት ቤቱ ድረ-ገፅ እንዲሁም በተማሪ መመርያ መፅሔት ላይ ይገኛል።

ሲሲኤስሲ ተማሪዎችን በሚመለምልበት እና በሚቀበልበት ሂደት ዉስጥ በዘር፥ በቀለም፥ በትዉልድ ሀረግ፥ በእምነት ወይም በሃይማኖት፥ በፆታ ፥ በፆታ ማንነት፥ በብሔር ፥ በወሲብ አም፥ በአዕምሮ ወይም በአካል ጉዳት፥ በእድሜ፥ በዘር ሐረግ፥ በሰዉነት ብቃት ደረጃ፥ በእንግሊዝኛ ወይም በዉጪ ቋንቋ ወይም ከዚህ ቀደም በነበረ የትምህርት ዉጤት አያዳላም፥ አይለይም። በምዝገባ ማዕቀፍ ዉስጥ የተጠየቁ የትዉልድ ቋንቋ ወይም የዘር ሐረግን ጨምሮ ሁሉም መረጃዎች ለማዳላት ወይም ለመለየት የታለሙ አይደሉም፤ ስለዚህም ለማዳላት/ለመለየት ጥቅም ላይ አይዉሉም።

ስለ ሲሲኤስሲ ተልዕኮ ለመረዳት ሁሉም አመልካቾች እና ወላጆቻቸዉ/አሳዳጊዎቻቸዉ በኦፐን ሃዉስ/ ክፍት ቤት ክፈለ-ጊዜ እንዲገኙ በአፅንዎት የሚያበረታታ ቢሆንም ሲሲኤስሲ ተማሪዎችን ወይም ቤተሰቦቻቸዉን በመረጃ ስብሰባዎች/ጥያቄና መልሶች ላይ መሳተፍን እንደ አንድ የቅበላ ወይም የማመልከቻ መስፈርት አይወስድም፤ እንዲገኙም አይገደዱም። ሲሲኤስሲ ለቅበላ የማመልከቻ ክፍያ አያስከፍልም ወይም ተማሪዎችን ለመመልመል የገንዘብ ድጎማን አይጠይቅም።

## C. የማመልከቻ እና የሎተሪ ሂደት

ሲሲኤስሲ ለመጪዉ የትምህርት ዓመት ሁልጊዜ በበልግ/ፎል ወቅት ማመልከቻዎችን መቀበል ይጀምራል። ሲሲኤስሲ ከጃንዋሪ 1 በፊት ማንኛዉንም መደበኛ የማመልከቻ ማብቂያ ቀን አያስቀምጥም ወይም ለመጨዉ የትምህርት ዓመት የተማሪዎች ምዝገባ የሚሆን ሎተሪ አያካሂድም። እንዲሁም የየዓመቱን መደበኛ የምልመላ እና የምዝገባ ሂደት ከማርች 15 በፊት ያጠናቅቃል። የሁሉም የሎተሪ ማመልከቻዎች የማብቂያ ጊዜ ቢያንስ ከአንድ ወር በፊት ይፋ ይደረጋል። ትምህርት ቤቱ ከሎተሪዉ ቀን አንድ ሳምንት በፊት ድረስ ማመልከቻዎችን ይቀበላል። ከሁሉም የቅበላ ሎተሪ አንድ ሳምንት በፊት ማሳሰቢያ ይሰጣል። አንድን ተማሪ ወደ ሎተሪዉ ሂደት ለማስገባት በሚገባ የተሞላ፥ ለማንበብ የማስቸግር የሎተሪ ማመልከቻ እና የነዋሪነት ማረጋገጫ ያስፈልጋል። ከተቀመጠዉ የማመልከቻ ማብቂያ ጊዜ በኋላ የሚመጡ የቅበላ ማመልከቻዎችን ትምህርት ቤቱ ተቀብሎ የሚያስቀምጣቸዉ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በተከታዩ ሎተሪ ላይ ያካትታቸዋል። ተጨማሪ ሎተሪዎች ላይ ከመሳተፍዎ በፊት ሲሲኤስሲ በመደበኛዉ ሎተሪ ዉጤት ላይ የተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ማስቀመጥ አለበት። ሁሉም አመልካቾች ማመልከቻቸዉን በሚያስገቡበት ወቅት የማሳቹሴትን ነዋሪዎች መሆን አለባቸዉ፤ እንዲሁም በሲሲኤስሲ ትምህርታቸዉን ለመቀጠል

617 354-0047 **P**
617 354-3624 **F**
enrollment@ccscambridge.org **E**
245 ቤንት ጎዳና
ካምብሪጅ, MA 02141
www.ccscambridge.org

በማሳቹሴትስ ነዋሪነታቸዉ መቀጠል አለባቸዉ። ቅበላ ተሰጥቶ ማረጋገጫ በሚደረግበት ወቅት አግባብነት ያለዉ የወቅቱ ነዋሪነት ማረጋገጫ ወይም ወንድም/እህት መኖሩን የሚያረጋግጥ ሰነድ አስፈላጊ ነዉ።

በሲሲኤስሲ ቻርተር እና በማሳቹሴትስ የቻርተር ትምህርት ቤት ህግ መሰረት አመልካቾች ቅበላ የሚያገኙት በእነዚያ የመመረጥ ደረጃ መሰረት ነዉ፡

1. <u>የማሳቹሴትስ ነዋሪዎች ሆነዉ የተማሪዉ/ዋ ወንድም/እህት በወቅቱ በሲሲኤስሲ የሚማር/የምትማር ከሆነ.</u> በዚህ ተቀባይነት የሚኖራቸዉ በተፈጥሮ ወይም በጉዲፈቻ አንድ ወላጅ ያላቸዉ ልጆች እና ከልጆቹ ዉስጥ አንዱ በማመልከቻዉ ወቅት እና በትምህርት ቤቱ ቆይታዉ ሁሉ የማሳቹሴትስ ነዋሪ የሆነና የነበረ መሆን አለበት። በዚህ ሎተሪ ዉስጥ በአንድ ቤት ዉስጥ የሚኖሩ የጋራ የተፈጥሮ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ የሌላቸዉ ልጆች እንደ ወንድም እና እህት አይቆጠሩም። አንድ ተማሪ "በማማር ላይ" ነዉ የሚባለዉ ቢያንስ አንድ ሙሉ ቀን በሲሲኤስሲ ካሳለፈ እና በሲሲኤስሲ ተማሪነቱን የቀጠለ ከሆነ ነዉ።

2. <u>የካምብሪጅ ነዋሪዎች፡</u> በካምብሪጅ ከተማ ነዋሪ ለሆኑ አመልካቾች የማመልከቻ ወቅት በማመልከቻ ማብቂያ ቀኑ የሚገደብ ይሆናል።

3. <u>ሌሎች የማሳቹሴትስ ነዋሪዎች፡</u> ነዋሪነታቸዉ ከካምብሪጅ ከተማ ዉጪ ነገር ግን በማሳቹሴትስ ግዛት ዉስጥ ያሉ አመልካቾች የማመልከቻ ወቅት በማመልከቻ ማብቂያ ቀኑ የሚገደብ ይሆናል። በዚህ ወቅት የማሳቹሴትስ የመጀመርያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቦርድ (ቢኤኤስኢ) በሲሲኤስሲ ተቀባይነት የሚያገኙ ተማሪዎችን በትምህርት ቤቱ የሚማሩ የካምብሪጅ ነዋሪ ተማሪዎች ከአጠቃላይ ተማሪዎች 80 በመቶ እና ከዚያ በላይ እስኪሆኑ ድረስ ለካምብሪጅ ነዋሪዎች ወይም ለተማሪዎች ወንድም/እህት ገድቧል።። ሲሲኤስሲ ከካምብሪጅ ከተማ ዉጪ የሚኖሩ እና ልጆቻቸዉ በሲሲሰኤስሲ የሚማር ወንድም/እህት የሌላቸዉን ቤተሰቦች በመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ እንዲመዘጉ እንዲሁም የመኖርያ ወይም የአድራሻ ለዉጥ ሲኖር እንዲያሳዉቁት ያበረታታል። ከላይ የተጠቀሱት የቅበላ ገደቦች የሚቀየሩ ከሆነ እናሳዉቆታለን።

በሎተሪዉ ቀን በሎተሪ ዉስጥ የተካተቱት ተማሪዎች ቁጥር ካሉት ክፍት ቦታዎች በታች ከሆኑ ማመልከቻቸዉን ያጠናቀቁት ተማሪዎች በቀጥታ በትምህርት ቤት ዉስጥ ቅበላ ያገኛሉ። ያሉት ክፍት ቦታዎች ደግሞ ብቁ ከሆኑ አመልካቾች የሚያንሱ ከሆነ ተማሪዎች በሎተሪ ሂደት ቅበላ እንዲያገኙ ይደረጋል። በመደበኛዉ የምዝገባ ሂደት ያሉትን ክፍት የቅበላ ቦታዎች መሙላት ካልተቻለ እንዳስፈላጊነቱ ቦታዎቹ ሙሉ እስኪሆኑ ድረስ ትምህርት ቤቱ ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ተጨማሪ የምዝገባ ሂደቶችን ያከናዉናል። ይህንንም ሂደት ነፃ እና ፍትሃዊ ለማድረግ ትምህርት ቤቱ ቢያንስ ከማመልከቻ ማብቂያ ቀኑ ከአንድ ወር በፊት ለህዝብ ይፋ ያደርጋል። ሁሉም የሚያስፈልጉ የሎተሪ ሂደቶች ለሁሉም ሎተሪዎች በጥብቅ ተፈፃሚ ይሆናሉ። በትምህርት ዓመቱ ዉስጥ አዳዲስ ክፍት ቦታዎች ከተፈጠሩ እነዚህን ክፍት ቦታዎች ለመሙላት እና የG.L. c. 70, § 89(n)ን ቅድመ-ሁኔታዎች ለማሟላት ሲባል ትምህርት ቤቱ የምዝገባ ሂደቱን በድጋሚ ሊያከናዉን ይችላል። 603 CMR 1.05(8). ሲሲኤስሲ በኮምፒዉተር እገዛ በዘፈቀደ የተፈጠሩ ልዩ የሎተሪ መለያ ቁጥሮችን ለእያንዳንዱ አመልካች ይሰጣል። ሁሉም አመልካቾች በዘፈቀደ በተዘረዘረዉ የደረጃ ዝርዝር ዉስጥ ከገቡ በኋላ በቅበላ ደረጃ መስጫ መስፈርቶች መሰረት ይደለደላሉ። በቢኤኤስኢ

617 354-0047 **P**
617 354-3624 **F**
enrollment@ccscambridge.org **E**
245 ቤንት ጎዳና
ካምብሪጅ, MA 02141
www.ccscambridge.org

የተቀመጠዉ የቅበላ መመርያ እስኪሟላ ድረስ በካምብሪች ነዋሪ የሆኑ አመልካቾች እና በሲሲኤስሲ የሚማር እህት/ወንድም ያላቸዉ ተማሪዎች ብቻ ቅበላ ያገኛሉ፡፡ የተቀሩት አመልካቾች በሙሉ በትምህርት ቤቱ የመጠባበቂያ ዝርዝር ፖሊሲ መሰረት ወደ መጠባበቂ ዝርዝሩ ይጨመራሉ፡፡ ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጃቸዉን የሎተሪ መለያ ቁጥር ከሎተሪዉ ከአንድ የስራ ቀን በፊት ትምህርት ቤቱን በማነጋገር ማግኘት ይችላሉ፡፡

የሎተሪ ማዉጣት ሂደቱ የሚከናወነዉ በ245 ቤንት ጎዳና፣ ካምብሪጅ, MA 02141 በሚገኘዉ ህንፃ በክፍል 235 ዉስጥ ህዝብ በተገኘበት በይፋ ይሆናል፡፡ የሎተሪ እጣ የማዉጣት ሂደቱ የሚከናወነዉ ኤሌክትሮኒክ በሆነ መንገድ ሲሆን የሂደቱን ፍትሃዊነት እና እጣ አወጣጥ ትክክለኛነት በገለልተኛ ወገን የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡ ቅበላ ያገኙ አመልካቾች በሙሉ በፖስታ እና/ወይም በኢሜል እና/ወይም በስልክ እንዲያዉቁ ይደረጋል፡፡ ከጃንዋሪ 1 እስከ ጁን 30 ድረስ ወላጆች/አሳዳጊዎች ቅበላ ማግኘታቸዉን የሚያሳዉቅ መልዕክት ከደረሰቻዉ ቀን በኋላ ባሉት ሁለት ሳምንታት (14 ቀናት) ዉስጥ ቅበላዉን መቀበላቸዉን በፅሁፍ ማረጋግጥ አለባቸዉ፡፡ ከጁን 30 በኋላ ቅበላ ያገኙ ተማሪዎች ደግሞ በአንድ ሳምንት (7 ቀናት) ዉስጥ ቅበላዉን ማረጋገጥ አለባቸዉ፡፡ ቅበላ ማግኘታቸዉን የሚገልፅ መረጃ ከተላከበት ቀን አንስቶ እስከ ማረጋገጫ ማስገቢያዉ ቀን ማብቂያ ድረስ ትምህርት ቤቱ የቅበላ ደብዳቤ በቤት አድራሻቸዉ መላኩን ለማስታወስ በስልክ፣ በፖስታ እና በኢሜል ቤተሰቦችን ያነጋግራል፡፡ ላገኙት ቅበላ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ የእሽታ ምላሽ አለመስጠት ቦታዉ ተቀምቶ በተጠባባቂ ዝርዝር ዉስጥ ላሉት እንዲሰጥ ያረጋል፡፡ ቅበላ አግኝቶ ምላሽ በሚሰጥበት ወቅት የወቅቱን የነዋሪነት ማረጋገጫ ወይም የሲሲኤስሲ ተማሪ ወንድም/እህት መኖሩን የሚያሳይ ማረጋገጫ መቅረብ አለበት፡፡

ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ የአቴንዳንስ ፖሊሲ መሰረት ከታለመዉ የትምህርት መጀመርያ ቀን አንስቶ በሚከተሉት አስር ቀናት ዉስጥ በትምህርት ቤት ዉስጥ የመገኘት ግዴታ አለባቸዉ፡፡ የማይገኙ ከሆነ ትምህርት ቤቱ ልጁን ከተቀበላቸዉ ተማሪዎች ዝርዝር አዉጥቶ ሌሎች ተማሪዎችን ከተጠባባቂዉ ዝርዝር መዉሰድ ይጀምራል፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዉ ከተጠባባቂዎች ዝርዝርም ይወጣል፤ በትምህርት ቤቱ ዉስጥ ምንም የተለየ ቦታ አይኖረዉም፡፡ ወላጆቹ ተማሪዉ በድጋሚ እንዲመዘገብ የሚፈልጉ ከሆነ ተማሪዉ በሚቀጥለዉ የማመልከቻ ዙር እንደገና ማመልከት አለበት፡፡

ምዝገባቸዉ የላካቸዉን ዲስትሪክት የትምህርት ወጪ አቅም የሚያልፍ ከሆነ ወይም በቢኢኤስኢ የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች የማያሟላ ተማሪዎች ቅበላ ላያገኙ ይችላሉ ነገር ግን በመጠባበቂያ ዝርዝር ዉስጥ ይቆያሉ፡፡ የትምህርት ወጪ የሚገድባቸዉ ነገር ግን በትምህርት ቤቱ የሚማር ወንድም/እህት ያላቸዉ ተማሪዎች እና የትምህርት ክፍያቸዉ በግዛቱ እንዲከፈል (አስፈላጊነቱ ታይቶ የሚረጋገጥ ነዉ) ሆኖ ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

## D. የመጠባበቂያ ዝርዝር ፖሊሲ

በአንድ ክፍል ላይ ያመለከቱ እና የክፍሉን የቅበላ መስፈርቶች ያሟሉ ነገር ግን ያሉት ክፍት ቦታ ከሞላባቸዉ ከሆነ እነዚህ አመልካቾች በሎተሪያቸዉ የደረጃ ቁጥር (በዘፈቀደ እጣ የሚሰጥ) መሰረት የነዋሪነት እና የተማረዉ/ዋ ወንድም/እህት የመኖራቸዉ ሁኔታ (በጊዜ ሂደት ሊቀየር የሚችሉ) ከግምት ዉስጥ ገብቶ በክፍል-ደረጃ የመጠባበቂያ ዝርዝር ዉስጥ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ በቢኢኤስኢ ላይ በተቀመጡት የምዝገባ ገደቦች ምክንያት የካምብሪጅ ነዋሪዎች ወይም በሲሲኤስሲ የሚማር ወንድም/እህት ያላቸዉ በተጠባባቂ ዝርዝር ዉስጥ ሊቆዩ የሚችሉ ሲሆን የካምብሪጅ ነዋሪዎች እና በሲሲኤስሲ የሚማር ወንድም/እህት ያላቸዉ ለቅበላ ብቁነታቸዉን ይዘዉ ሊቆዩ ይችላሉ፡፡

617 354-0047 **P**
617 354-3624 **F**
enrollment@ccscambridge.org **E**
245 ቤንት ጎዳና
ካምብሪጅ, MA 02141
www.ccscambridge.org

አንድ ተማሪ ከሲሲኤስሲ ከወጣ ወይም የቅበላ ማመልከቻዉን ከሰረዘ ከላይ በተገለፀዉ የሎተሪ ሂደት መሰረት በዚያ ክፍል ደረጃ የተጠባባቂዎች ዝርዝር መጀመርያ ላይ ለተቀመጠዉ ተማሪ ቦታዉ ይሰጥና በስልክ ወይም በፅሁፍ እንዲያዉቅ ይደረጋል። ከጃንዋሪ 1 እስከ ጁን 30 ድረስ ወላጆች/አሳዳጊዎች ቅበላ ማግኘታቸዉን የሚያሳዉቅ መልዕክት ከደረሰቻዉ ቀን በኋላ ባሉት ሁለት ሳምንታት (14 ቀናት) ዉስጥ ቅበላዉን መቀበላቸዉን በፅሁፍ ማረጋግጥ አለባቸዉ። ከጁን 30 በኋላ ቅበላ ያገኙ ተማሪዎች ደግሞ በአንድ ሳምንት (7 ቀናት) ዉስጥ ቅበላዉን ማረጋገጥ አለባቸዉ። ከዚህ ቀደም በነበረ ምዝገባ መጠባበቂያ ዝርዝር ላይ የተቀመጡ ተማሪዎች እያሉ በ 603 CMR 1.05 እንደተገለፀዉ የምዝገባ የአመራረጥ ዘዴ እስካልተለወጠ ድረስ ማንም ሌላ ተማሪ በቅድሚያ ቅበላ አያገኝም። ተመዝግቦ የተወ ወይም ቅበላ አግኝቶ በተጠቀሰዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ የስምምነት ምላሽ ያልሰጠ ተማሪ ከመጠባበቂያ ዝርዝሩ በዘላቂነት እንዲፋቅ ይደረጋል። ወደፊት በሲሲኤስሲ ለማማር ከፈለገም እንደገና ለቅበላ ማመልከት ይኖርታል። የመጠባበቂያ ዝርዝሩ በየዓመቱ የሚቀመጥ/የሚሸጋገር አይደለም። አንድ ከሲሲኤስሲ የለቀቀ ተማሪ እንደገና ወደ ሲሲኤስሲ መመለስ ቢፈልግ ለምዝገባ/ለቅበላ እንደገና ማመልከት አለበት።

ሲሲኤስሲ ወደ ሎተሪ ገብተዉ ነገር ግን ቅበላ ያላገኙትን ተማሪዎች ትክክለኛ መረጃ እነዚህም ስም (የራስ፣ የአባት፣ የአያት/የቤተሰብ)፣ የትዉልድ ቀን፣ የመኖርያ አዉራጃ እና ከተማ፣ የክፍል ደረጃ ፣ የቤት አድራሻ እና የስልክ ቁጥርን በሚገባ አደራጅቶ ይይዛል/ያስቀምጣል።

**E. መልሶ-መሙላት**

ትምህርት ከተጀመረ በኋላ ማንኛዉም የ6ኛ፣ 7ኛ ፣ 8ኛ ወይም 9ኛ ክፍል ተማሪ በማንኛዉም ምክንያት ትምህርቱን መከታተል ካቆመ ትምህርት ቤቱን በሱ ቦታ የተፈጠረዉን ክፍት ቦታ እስከ ፌብሩዋሪ 15 ድረስ ለመሙላት ጥረት ያደርጋል። የክፍል ደረጃዉ 10፣ 11 ወይም 12 ካልሆነና ክፍት ቦታዉ እስከ ፌብሩዋሪ 15 ድረስ ካልተሟላ ወደ ተከታዩ የክፍል ደረጃ እንዲተላለፍ ይደረጋል። የቻርተር ትምህርት ቤቱን የቅበላ እዉቅና ተቀብለዉ የተመዘገቡ ነገር ግን አንድ ጊዜም ቢሆን በክፍሉ ያልተገኙ ተማሪዎች ቦታዎች ከዚህ አሰራር ዉጪ ናቸዉ። ትምህርት ቤቱ የመጠባበቂያ ዝርዝርን የሚያስቀምጠዉ ተማሪዎቹ ላመለከቱበት የትምህርት አመት ብቻ ነዉ። በእያንዳንዱ የምዝገባ ዙር ከፌብሩዋሪ 15 በኋላ በመጠባበቂያ ዝርዝሩ ላይ ያሉ ሁሉም ማመልከቻዎች ዋጋ አይኖራቸዉም። ለተከታዩ አመት በትምህርት ቤቱ ተቀባይነት ማግኘት የሚፈልጉ ተማሪዎች እንደገና ማመልከቻ ማስገባት እና እንደገና በሎተሪ ሂደት ዉስጥ መሳተፍ ይኖርባቸዋል።

**F. ነባር ተማሪዎች**

የሲሲኤስሲ ነባር ተማሪዎች እንደገና እንዲያመለክቱ እና እንደገና እንዲመዘገቡ አይጠበቅባቸዉም። አንድ ተማሪ በትምህርት ጊዜ ክፍል ካልተገኘ በአቴንዳንስ ፖሊሲዎች እና ሂደቶች መሰረት እርምጃ ይወሰዳል።

**G. የተማሪን መረጃ መግለጥ (ለ3ኛ ወገን)**

በ M.G.L Chapter 71, Section 89(f); CMR 603 1.05(f) ላይ እንደተገለፀዉ የካምብሪጅ የማህበረሰባዊ ቻርተር ትምህርት ቤት የተማሪዎች የምልመላ እና የአያያዝ እቅድ የሚኖረዉና ተግባራዊ የሚያደርግ ይሆናል። ሲሲኤስሲ የተማሪዎቹን ግላዊነት/ገመና የሚያከብር ሲሆን በህግ ካልታዘዘ በስተቀር የተማሪን መረጃ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ አይሰጥም። በ Statute M.G.L. Chapter 71, Section 89(g) መሰረት ወላጅ የልጁ መረጃ በትምህርት-ቤቱ

617 354-0047 **P**
617 354-3624 **F**
enrollment@ccscambridge.org **E**
245 ቤንት ጎዳና
ካምብሪጅ, MA 02141
www.ccscambridge.org

እንዲቀር እስካልጠየቀ ድረስ ሲሲኤስሲ በሲሲኤስሲ የከተማ ትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች ጥያቄ መሰረት የፖስታ አድራሻ ዝርዝሩን በግዛቱ-እዉቅና ላለዉ ሶስተኛ ወገን ፖስታ ቤት ይሰጣል። ወላጆች በenrollment@ccscambridge.org የኢሜል አድራሻ ኢ-ሜይል በማድረግ ወይም ለትምህርት ቤቱ በ617-354-0047 ስልክ ቁጥር በመደዉል ይህንን ጥያቄአቸዉን ማቅረብ ይችላሉ። ይህ መረጃ በተማሪዎች እና በወላጆች መፅሄት ላይ ይገኛል።

**H. የእድገት እቅድ**

ከፌብሩዋሪ 27 2017 ጀምሮ የመጀመርያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቦርድ የሲሲኤስሲን የአዲስ ተማሪ ቅበላዎችን ለካምብሪጅ ነዋሪዎች እና በትምህርት ቤቱ የሚማር ወንድም/እህት ላላቸዉ ብቻ ገድቦታል። በአሁኑ ሰዓት ለሲሲኤስሲ ቅበላ የሚያመለክቱ ወይም በቅበላ በመጠባበቂያ ዝረዝር ላይ የሚገኙ እና ከካምብሪጅ ዉጪ ነዋሪ የሆኑ እንዲሁም በሲሲኤስሲ የሚማር ወንድም/እህት የሌላቸዉ አመልካቾች ወደ ሲሲኤስሲ **ቅበላ አያገኙም/አይሰጣቸዉም**። በቻርተር ትምህርት ቤቱ ቅድመ-ሁኔታዎች መሰረት በሲሲኤስሲ ከሚማሩ አጠቃላይ ተማሪዎች 80 በመቶ እና ከዚያ በላይ የሚሆኑት የካምብሪጅ ነዋሪዎች እስኪሆኑ ደረስ የመጀመርያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቦርድ ይህንን ገደብ አስቀምጧል። ከላይ የተቀመጠዉ ገደብ የሚቀየር ከሆነ የምናሳዉቃችሁ ይሆናል።

ሲሲኤስሲ ከካምብሪጅ ከተማ ዉጪ የሚኖሩ እና ልጆቻቸዉ በሲሲሰኤስሲ የሚማር ወንድም/እህት የሌላቸዉን ቤተሰቦች በመጠባበቂያ ዝርዝር ላይ እንዲመዘጉ እንዲሁም የመኖርያ ወይም የአድራሻ ለዉጥ ሲኖር እንዲያሳዉቁት ያበረታታል።

ሲሲኤስሲ በተሻሻለዉ የትምህርት ቤቱ ቻርተር የማቴርያል ተርም ከተቀመጠዉ የቅበላ ጣርያ እና የእድገት እቅድ በላይ ተማረዎችን አይቀበልም። በአንድ የትምህርት አመት በቻርተር ትምህርት ቤት ዉስጥ የሚማሩ ተማሪዎች አጠቃላይ ብዛት በ603 CMR 1.08(5) መሰረት በባለፈዉ ስፕሪንግ/ፀደይ ለትምህርት ክፍሉ በትምህርት ቤቱ የቅድመ-ምዝገባ ሪፖርት ላይ ከተቀመጠዉ የአጠቃላይ የተማሪዎች ቁጥር ማለፍ አይችልም።

| ክፍሎች | FY18 | FY19 | FY20 | FY21 | FY22 | FY23 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | 37 | 45 | 45 | 45 | 45 | 60 |
| 7 | 65 | 62 | 65 | 64 | 63 | 60 |
| 8 | 62 | 65 | 65 | 65 | 64 | 63 |
| 9 | 46 | 62 | 65 | 65 | 65 | 64 |
| 10 | 50 | 43 | 58 | 61 | 61 | 61 |
| 11 | 54 | 47 | 41 | 55 | 57 | 57 |
| 12 | 51 | 51 | 44 | 38 | 51 | 54 |
| **አጠቃላይ** | 365 | 375 | 383 | 393 | 407 | 420 |

617 354-0047 **P**
617 354-3624 **F**
enrollment@ccscambridge.org **E**
245 ቤንት ጎዳና
ካምብሪጅ, MA 02141
www.ccscambridge.org

ከላይ የተጠቁት አሃዞች በብሔራዊ የቅበላ መዋዢቆች (ለምሳሌ እንደ ነባር ቅበላዎች) ምክንያት ሊለዋወጡ የሚችሉ ግምታዊ ትንበያዎች ናቸዉ። በአረንጓዴ የተከበቡ ዉጤቶች እስከ ፌብሩዋሪ 15 ድረስ በሚወጡ ክፍት የስራ መደቦች ሊሞሉ ይችላሉ።